መልእክት ስድስት

**እንደ የሕያው እግዚአብሔር መቅደስ**
**ለክርስቶስ አካል መገንባት**
**ከማደሪያው ድንኳን የቤተ ክርስቲያን ሕይወት**
**ወደ መቅደሱ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት**
**ከጌታ ጋር መቀጠል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ማቴ. 12፡3-4፣ 42፤ ዮሐ. 14፡21፣ 23፤
ሮሜ 8፡28-29፤ መዝ. 27፡4፤ 36፡8-9፤ 43፡4፤ 84፡4-5

I. **ጌታ በውስጣችን በነፍስ ምድረ በዳ ካለው የማደሪያው ድንኳን የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በመንፈሳችን እንዳለው እንደ መልካሚቱ ምድር እውነታ ከክርስቶስ፣ ሁሉን-ካካተተው መንፈስ ጋር ወደ መቅደሱ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ለመቀጠል እየናፈቀ ነው—ዕብ. 6፡1፤ ኢያ. 3፡14-17፤ ዘዳ. 8፡8፤ ኤፌ. 2፡21-22፤ ቆላ. 1፡12፤ 2፡6-7።**

II. **የማደሪያው ድንኳን እና መቅደሱ የቤተ ክርስቲያንን ሁለት ገጽታዎች በምሳሌ ያሳያሉ፡-**

ሀ. አንደኛ ነገሥት 8፡1-11 የማደሪያው ድንኳን ከመቅደሱ ጋር በአንድ ላይ ተጣምሮ እንደነበር ያሳያል፤ የማደሪያው ድንኳን በምድረ በዳ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ተንቀሳቃሽ ቅድመ-ጠቋሚ የነበረ ሲሆን፣ መቅደሱ በምሳሌ የእግዚአብሔር ግንባታ መጠናቀቅ ነበር።

ለ. መቅደሱ እንደ የማደሪያው ድንኳን መተለቅ የቤተ ክርስቲያንን መጠንከር እና መጽናት ያመለክታል፣ በመቅደሱ ውስጥ ያሉት ዕቃዎች መታደስ እና መተለቅ የቅዱሳንን የክርስቶስ ልምምድ መታደስ እና መተለቅ ያመለክታሉ፤ የመቅደሱ እና በመቅደሱ ውስጥ ያለው የቅድስተ ቅዱሳን ልኬቶች የማደሪያው ድንኳን ሁለት እጥፍ ነበሩ፤ በተጨማሪም፣ ከታቦቱ ውጪ፣ የዕቃዎቹ ልክ እና ቁጥር ለተለቀ መገለጡ እጅግ እንዲተልቁ ተደርገው ነበር—6፡2፣ 20፤ 2 ዜና 4፡1-8፤ ተዛ. ዘጸ. 26፡3፣ 16፣ 18፣ 22-24፤ 33።

ሐ. የማደሪያው ድንኳን በምድር ላይ ያለችውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን፣ ወይም በአጥቢያዎች ያለችውን ቤተ ክርስቲያኑን በምሳሌ የሚያሳይ ሲሆን፣ መቅደሱ ቤተ ክርስቲያንን እንደ የክርስቶስ አካል እውነታ ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ክቡር ግብ ወደ ሆነው ወደ አካሉ እውነታ እኛን ለማምጣት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውድ የከንውን ሂደቶች ናቸው—ኤፌ. 1፡22-23፤ ተዛ. ራእ. 21፡10-11።

መ. ልዩና ብቸኛው አገልግሎት ለእግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ ምስክር ነው፣ የእግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ ምስክር፣ የክርስቶስ አካል እውነታ እውን የሚሆነው በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ነው—ዘጸ. 25፡22፤ 38፡21፤ ራእ. 1፡2፣ 9፤ ተዛ. ኤፌ. 4፡4፤ ዮሐ. 16፡13።

ሠ. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12 የተገለጠው አካል አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚገባ ምስክር ነው፤ የአካሉ ምስክር ነው፤ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የክርስቶስን አካል እውነታ የምትገልጥ ምስክር መሆን አለባት—ቁ. 14-18፣ 20።

ረ. ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው ለአንድነት ምስክር ነው፤ "አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን" ብለን ስናመለክት አጽንኦት እየሰጠን ያለነው ለቤተ ክርስቲያን እንጂ "ለአጥቢያዊ-ነት" አይደለም፤ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸው ሕይወት የአንድነት ሕይወት ነው—ዮሐ. 17፡11፣ 21፣ 23፤ ራእ. 1፡10-12።

ሰ. የክርስቶስ አካል እውነታ ምስክር የእግዚአብሔር የመጨረሻ ምለሳ ነው—ክርስቶስ ሁሉ ነገራችን ከሆነበት፣ ከክርስቶስ አካል አንድነት እና የአካሉ ብልቶች ሁሉ ከማገልገላቸው ጋር የሆነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ምለሳ ነው—1 ጢሞ. 1፡3-6፤ 6፡3-5፤ ዕብ. 13፡9፤ ኤፌ. 1፡17፤ 3፡2፣ 8-11፤ 16-21፤ 4፡1-6፣ 16።

III. **የዮሐንስ ወንጌል ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሕያው እግዚአብሔር መቅደስ መገንባት የክርስቶስ ወንጌል እንደ ሕይወት ነው፤ ይህ የግንባታ ሥራ የሚከናወነው የተሰቀለውን እና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ እንደ ሕይወት ዛፍ በመለማመዳችን እና በመደሰታችን በኩል ነው—ራእ. 2፡4-7፤ 1 ጴጥ. 2፡24፤ ዮሐ. 11፡25፤ 6፡57፣ 63፤ 2 ቆሮ. 6፡16፡-**

ሀ. የሕይወት መርህ ሞትን ወደ ሕይወት መለወጥ ነው (ዮሐ. 2፡1-11)፣ የሕይወት አላማ ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር ቤት፣ እንደ እግዚአብሔር መቅደስ መገንባት ነው (ቁ. 12-22)፤ ስለዚህ፣ ጌታ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ" ብሎ አወጀ (ቁ. 19)።

ለ. በሞቱ፣ በመስቀል ላይ በቁሳዊ አካሉ መጥፋት በኩል እኛን ለመዋጀት እና ለማጽደቅ መተላለፋችንን እና በደላችንን ተሸከመ፣ ሞቱም ደዌያችንን ለመፈወስ ነበር—ኢሳ. 53፡4-6፤ ሮሜ 3፡23-26፤ 1 ጴጥ. 2፡24።

ሐ. የጌታ ቁሳዊ አካል መጥፋቱ የሞት ኃይል ያለው የዲያቢሎስ መጥፋትም ጭምር ነበር፤ በመስቀል ላይ ሲሞት አሮጌው ፍጥረት፣ አሮጌው ሰው፣ ሥጋ፣ ሰይጣን፣ ኃጢአት፣ ኃጢአቶች እና ዓለም በመስቀል ላይ ተሰቀሉ፤ ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር ዓይኖች፣ ከክርስቶስ መሰቀል በኋላ፣ መላው አጽናፍ-ዓለም ጸድቷል—ዕብ. 2፡14፤ ሮሜ 6፡6፤ ገላ. 2፡20፤ 5፡24፤ ዮሐ. 1፡29፤ 3፡14፤ 6፡70-71፤ 12፡31፤ ማቴ. 16፡23፤ 1 ቆሮ. 15፡3።

መ. የጌታ ቁሳዊ አካል መጥፋቱ እና በሦስት ቀናት መነሣቱ ብዙ አማኞቹን የእግዚአብሔር ርቢ ለማድረግ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር መለኮታዊ እሳት ወደ ብዙ አማኞቹ ለመልቀቅ እና ለማደል፣ እንደ ስንዴ ቅንጣት መሞቱ እና ከሞት መነሣቱ ጭምር ነበሩ—ዮሐ. 12፡24፤ ሉቃ. 12፡49-51።

ሠ. በክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ በኩል፣ ፣ አጽናፍ-ዓለማዊውን የእግዚአብሔር መቅደስ፣ የሕያው እግዚአብሔር ቤት የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን፣ ይህም ብዙዎች የተካተቱበት እና ምሥጢራዊ አካሉን ለመሆን፣ ቁሳዊ አካሉ ጨምሯል—1 ቆሮ. 3፡16-17፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ 1 ጴጥ. 2፡5፤ ኤፌ. 2፡21-22።

ረ. ብዙዎቹ መኖሪያዎች የእግዚአብሔር መቅደስ የሆኑት ብዙዎቹ የክርስቶስ አካል ብልቶች ናቸው—ዮሐ. 14፡2፣ 23፤ ሮሜ 12፡5፤ 1 ቆሮ. 3፡16-17።

ሰ. በክርስቶስ ሕይወት-ለቃቂ ሞት እንደ ፈሩት ብዙ ስንዴዎች እና በክርስቶስ ሕይወት-አዳይ ትንሣኤ እንደፈሩት የክርስቶስ ምሥጢራዊ አካል ብዙ መኖሪያዎች፣ በሸክላ ዕቃዎቻችን ውስጥ ባለው ውድ መዝገብ ኃይል ለትንሣኤው ሕይወት መገለጥ የተሰቀለ ሕይወት በመኖራችን እርሱን ፈጽመን የምንወድ መሆን አለብን—ዮሐ. 14፡21፣ 23፤ ሮሜ 8፡28-29፤ 2 ቆሮ. 4፡7-18፤ 12፡7-9።

## IV. ዳዊት እና ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ግንባታ ክርስቶስን በሁለት ገጽታዎች በምሳሌ ያሳያሉ፡-

ሀ. ዳዊት ክርስቶስን ከተሠግዎው ጀምሮ የአምላክ-ሰው ኑሮውን እና መከራዎቹን ጨምሮ እስከ ሞቱ (ከግርግም እስከ መስቀሉ) በምሳሌ ያሳያል—ማቴ. 12፡3-4፤ 22፡41-46።

ለ. ሰሎሞን ክርስቶስን በክብር በሆነው ትንሣኤው በውስጣችን እንዳለው ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ (መንገሡን እና በምድር ላይ በመንግሥቱ ላይ ለመግዛት ሁለተኛ መምጣቱን ጨምሮ) ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር መቅደስ ለመገንባት የእግዚአብሔርን የጥበብ ቃል መናገሩን በምሳሌ ያሳያል—12፡42፤ 2 ዜና 1፡10፤ 1 ቆሮ. 1፡24፣ 30፤ 12፡8።

ሐ. እግዚአብሔር "ሲመሰክርለትም፡- እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ" ሐዋ. 13፡22፤ ዳዊት "በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ አገለገለ" (ቁ. 36)፤ እርሱ እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው ነበር (1 ሳሙ. 13፡14) ምክንያቱም ሰሎሞን "አባቴም ዳዊት ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ስም ቤት ይሠራ ዘንድ በልቡ አሰበ" ብሎ እንደመሰከረው ነውና (1 ነገ. 8፡17-20፤ ተዛ. ኤፌ. 1፡5፣ 9፤ 1 ቆሮ. 12፡12-27—ቁጥር 13 ላይ የግርጌ ማስታወሻ 2ን ተመልከቱ)።

መ. ዳዊት ከልጅነቱ ጀምሮ መከራ ቢቀበልም፣ በመከራው ግን የግንባታ ዕቃዎቹን አዘጋጀ፣ ለመቅደሱ መገንባት ተገቢውን ስፍራ አገኘ፣ ገንቢውን ሰሎሞንን እና ረዳቶቹን ሁሉ አዘጋጀ—1 ዜና 21፡18-30፤ 2 ዜና 3፡1፤ 1 ዜና 28፡9-11፣ 20-21።

ሠ. ዳዊት ለእግዚአብሔር መቅደስ ግንባታ ዕቃዎቹን በብዛት ማዘጋጀቱ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ፍሲጋ የሌላቸውን ብልጥግናዎቹን ማቅረቡን በምሳሌ ያሳያል—18፡7-11፤ 22፡2-5፣ 14-16፤ 28፡2፤ 29፡2-9፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡8-10።

ረ. ዳዊት በመከራው (1 ዜና 22፡1፣ 14)፣ በፈተናዎቹ እና በውጊያዎቹ ድሎች [ዕቃዎቹን] ማዘጋጀቱ ክርስቶስ በፈተናዎቹ እና ከሰይጣንና ከጨለማ ኃይሉ ጋር በመዋጋት ሕይወቱ ድል ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ግንባታ የበለጠገ አቅርቦቱን በምሳሌ ያሳያል (ማቴ. 4፡4፣ 7፣ 10)።

ሰ. ለዳዊት የተሰጠው የመቅደሱ ምሳሌ "በመንፈሱ ላሰበው ሁሉ ምሳሌ" ነበር (1 ዜና 28፡12)፤ "ዳዊትም፡- የሥራውን ሁሉ ምሳሌ አውቅ ዘንድ ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ተጽፎ መጣልኝ አለ" (ቁ. 19፤ ተዛ. 2 ዜና 3፡3)፤ በሰሎሞን የተገነባው መቅደስ በዚህ ምሳሌ መሠረት ነበር (1 ዜና 28፡11)።

ሸ. ዳዊት ከእግዚአብሔር መቅደስ ጋር በተገናኘ የእስራኤልን አገልግሎቶች በስርዓት ማዘገጃጀቱ (6፡31-48፤ ምዕ. 23—26) መንፈስ በአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች በስርዓት ማዘገጃጀቱን በምሳሌ ያሳያል፣ ክርስቶስ እንደ አካሉ ራስ በአካሉ ውስጥ ብልቶቹ ሁሉ እንዲጠብቁት ስርዓትን ማቆሙንም በምሳሌ ያሳያል (ቁ. 18፤ 14፡40)።

ቀ. የቤተ ክርስቲያን ንድፍ የትንሣኤ መንፈስ—ሁሉን-ያካተተው፣ ሕይወት-የሚሰጠው፣ የተቀመመው፣ በውስጥ የሚያድረው መንፈስ—ነው፤ በመንፈሳችን ውስጥ ባለው በትንሣኤ መንፈስ ስንኖር፣ በዳዊት ንድፍ መሠረት ሰሎሞን መቅደሱን የመገንባቱ እውነታ (ከክርስቶስ የአምላክ-ሰው ኑሮ፣ ሞት እና ትንሣኤ ስራዎች ሁሉ ጋር) በውስጣችን ይፈጸማል—ዮሐ. 2፡19፤ ፊልጵ. 1፡19፤ ኤፌ. 1፡17፤ 2፡22፤ 3፡5፣ 16፤ 4፡23፤ 5፡18፤ 6፡18።

በ. የሰሎሞን ስም “ሰላም” ማለት ሲሆን፣ ትርጓሜውም ቤተ ክርስቲያን የምትገነባው በክርስቶስ በሰላም እንደ ሆነ እንደ “የዕረፍት ሰው”፣ ያለ ምንም ጫጫታ ነው ማለት ነው—1 ዜና 22፡9፤ ሐዋ. 9፡31፤ ኤፌ. 4፡29-32፦

1. ለመቅደሱ ግንባታ ጥቅም ላይ የዋለው እያንዳንዱ ድንጋይ፣ በመርህ ደረጃ፣ በተራሮች ላይ የተጠረበ እና የተዘጋጀ ነበር፤ ስለዚህ፣ የመራጃ፣ የመጥረቢያ እና የብረት ዕቃ ድምጽ አልተሰማም፣ መቅደሱም በጸጥታ ተገነባ—1 ነገ. 5፡15-18፤ 6፡7።
2. አንድ በጌታ ያልታደበ ወንድም (ያለማቋረጥ የሚያወራ፣ ጥሩ አድማጭ ያልሆነ እና ከዚያም የተነካ ያልታደሰ አእምሮ ያለው) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን በመራጃ፣ በመጥረቢያ እና በብረት ዕቃ ድምጽ ትሞላለች፤ አንዳንዱ “ጫጫታ” የተወሰኑ ቅዱሳን አንዳቸው የሌላቸውን ጸሎት ከንቱ ለማድረግ በመጸለይ እርስ በርስ ሲጣሉ ሊሆን ይችላል—ተዛ. ኢሳ. 50፡4-5፤ ኤፌ. 4፡23።
3. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሌሎችን ነቀፋ፣ ፍርድ፣ ክርክር እና ተቃውሞ ከሰማን፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መሸሽ፣ ማለትም፣ ወደ መንፈሳችን ውስጥ መሸሽ እና መዞር አለብን፤ መቅደሱ የሚገነባው በጸጥታ ነው—ገላ. 6፡17-18፤ ኢሳ. 30፡15።
4. ታቦቱ ዐርፎ ከተቀመጠ በኋላ ዳዊት ለዝማሬ አገልግሎት በያሕዌ ቤት ያቆማቸው ሰሎሞን የያሕዌን ቤት በኢየሩሳሌም እስኪሠራ ድረስ በመገናኛ ድንኳን ማደሪያ ፊት እያዜሙ ያገለግሉ ነበር—1 ዜና 6፡31-32።

ተ. እንደ እግዚአብሔር ቤት በቤተ ክርስቲያን አዕማድ ወደ መሆን ፍጹማን ለመደረጋችን ንጉሡ ራሱን ወደ ውስጣችን እንዲገነባ እርሱን እንደ ተሰቀለው እና ከሞት እንደተነሣው ክርስቶስ እየተደሰትን “ከንጉሡ ጋር ለሥራው እናድራለን”—ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ መዝሙር #904፤ 1 ዜና 4፡23፤ 1 ነገ. 7፡17፣ 21፤ ራእ. 3፡12።

ቸ. ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ እንደ ትንሣኤ ኃይል እና በሂደት ያለፈውን የሦስታንዱ አምላክ (እውነተኛውን እና የሚበልጠውን ሰሎሞን) ከሞት የሚያስነሣ እና ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ በመደሰት፣ ስለ አካሉ (እውነተኛው እና የሚበልጠው መቅደስ) ሞቱን ለመምሰል (እንደ እውነተኛው እና የሚበልጠው ዳዊት) እንደ ጸሎት ሰው ከአምላክ-ሰው ኑሮው ጋር በክርስቶስ መከራዎች ኅብረት መሳተፍ እንችላለን—ፊልጵ. 3፡10፤ ሮሜ 8፡11፤ ማቴ. 12፡3-4፣ 42፤ ዮሐ. 2፡19-22፤ 2 ቆሮ. 6፡16።

## V. እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሕያው እግዚአብሔር መቅደስ የሚገነባበት ሃሳቦቹ እና መንገዶቹ ከእኛ ከፍ ያሉ ናቸው፤ የእኛን መንገዶች እና ሃሳቦች መተው እና እንደ ሕያው እግዚአብሔር መቅደስ በቤተ ክርስቲያን እርሱን የመደሰትን መንገድ ለመከተል ወደ አምላካችን ያሕዌ መመለስ ያስፈልገናል—ዘፍ. 2፡9፤ ዮሐ. 6፡35፣ 57፣ 63፤ ኢሳ. 55፡6-13፤ 57፡20፤ ዮሐ. 1፡14፤ 2፡19፤ 3፡34፤ 17፡17፤ ኤፌ. 5፡26፤ 2 ቆሮ. 3፡15-18፤ 6፡16፤ ሮሜ 8፡28-29፤ ራእ. 22፡1-2፦

ሀ. እንደ እግዚአብሔር ልጆች፣ ጽንሰ-ሃሳባችንን መለወጥ እና የእግዚአብሔር መሻት ለድሰታችን ራሱን መስጠት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል—መዝ. 36፡8-9፤ 16፡11፤ 19፡8፤ 27፡6፤ 42፡4-5፤ 48፡2፤ 63፡7፤ 66፡1-2፤ 81፡1፤ 89፡15-18፤ 95፡1-2፤ 100፡1-2፤ 126፡1-6፤ ነህ. 8፡10፤ 1 ዮሐ. 1፡3-4፦

1. ፍሬ ማፍራት እግዚአብሔርን መደሰት ነው—ዮሐ. 15፡7-11።
2. ጸሎት እግዚአብሔርን መደሰት ነው—ሰቆ. 3፡55-56፤ ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ መዝሙር #255።
3. ቃሉን ማገልገል እግዚአብሔርን መደሰት ነው—ዮሐ. 6፡57፣ 63፤ 7፡37-39፤ 1 ቆሮ. 15፡10፤ 2 ቆሮ. 3፡1-6፣ 18፤ 2፡17፤ 13፡3፤ ኤፌ. 3፡2፤ 1 ጴጥ. 4፡10-11፤ ኤር. 15፡16፤ ሕዝ. 3፡1-4፤ ኢሳ. 55፡8-11።
4. ወንጌል መስበክ እግዚአብሔርን መደሰት ነው—ዮሐ. 4፡10፣ 13-14፣ 31-34።
5. ምሪቱን መቀበል እግዚአብሔርን መደሰት ነው—ዘጸ. 33፡14።

ለ. ድል ነሺዎች እንሆን ዘንድ የክርስቲያን ሕይወትን የመኖር ምሥጢሩ እግዚአብሔርን እንደ ሕይወት ዛፍ የመደሰትን መንገድ መከተላችን ነው፤ እግዚአብሔር ምንም እንድናደርግለት አልወጠነም፤ ብቸኛው መሻቱ ለድሰታችን ራሱን ለእኛ እንደ ምግብ መስጠት ነው—ዘፍ. 2፡9፤ ራእ. 2፡7።

ሐ. ያሕዌ መልካም እንደሆነ በእግዚአብሔር ቤት፣ በእግዚአብሔር መቅደስ፣ ማለትም፣ በክርስቶስ (ዮሐ. 2፡19-22)፣ በቤተ ክርስቲያን (1 ጢሞ. 3፡15፤ 1 ቆሮ. 3፡16-17፤ 2 ቆሮ. 6፡16)፣ በመንፈሳችን (ኤፌ. 2፡22) ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ በሆነ መልኩ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም (ራእ. 21፡22) ቀምሰን እናያለን (መዝ. 34፡8)።

መ. የእግዚአብሔርን መኖሪያ ቤት፣ መቅደሱን እና ክብሩ ለመገለጥ የሚኖርበትን፣ የሚቀይበትን መውደድ አለብን—መዝ. 26፡8፤ 84፡1፤ 29፡9፤ ኤፌ. 3፡20-21።

ሠ. “እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፥ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ” (መዝ. 27፡4)፤ የእግዚአብሔር ቤት ለአብ መገለጥ፣ እርካታ እና ዕረፍት የሆነ የተለቀው፣ አጽናፍ-ዓለማዊው፣ የመለኮት-ስብዕና መካተት ነው (ዮሐ. 14፡2፣ 20፣ 23)።

ረ. እንደ የቤቱ ስብ እንዲሞላን፣ እንደ ደስታዎች ወንዝ ጥማችንን እንዲያረካን እና እንደ ሕይወት እና ብርሃን ምንጭ እንዲመግበን እና አብርሆት እንዲሰጠን በክርስቶስ፣ በቤተ ክርስቲያን እና በመንፈሳችን፣ “የሚገኘውን አምላክ” እንደሰተዋለን—መዝ. 36፡8-9።

ሰ. “ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ፥ ጕልማስነቴንም ደስ ወዳሰኘት ወደ አምላኬ እገባለሁ፤ አቤቱ አምላኬ፥ በበገና አመሰግንሃለሁ”—43፡4።

ሸ. በእግዚአብሔር ቤት፣ በእግዚአብሔር መቅደስ እግዚአብሔር የፊታችን መድኃኒት መሆን ይችል ዘንድ (42፡11) የእግዚአብሔርን ፊት ማዳን፣ የእግዚአብሔርን መገኘት እንደሰታለን (ቁ. 5)።

**VI. “በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው፤ ለዓለምና ለዘላለምም ያመሰግኑሃል። አቤቱ፥ እርዳታው ከአንተ ዘንድ የሆነለት፥ በልቡም የላይኛውን መንገድ የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው”—መዝ. 84፡4-5፡-**

ሀ. “ስምህንም ለዘላለም ዓለምም አመሰግናለሁ”—145፡2።

ለ. “በሕይወቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ በምኖርበት ዘመን ሁሉ ለአምላኬ እዘምራለሁ”—146፡2።

ሐ. “አንተ ግን ቅዱሱ ነጋሢ/ የእስራኤልም ምስጋና ነህ" —22፡3 (አ.መ.ት.)።

መ. “እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት”—ዕብ. 13፡15፤ ፊልጵ. 2፡11።

© 2022 Living Stream Ministry